# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 42 ቁ. 5 — መጋቢት/ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም


## የየካቲት ጥያቄዎች እስካልተመለሱ ፤ የሕዝቡ ትግል ይቀጥላል !

በዓይነቱም ሆነ በይዘቱ በሌሎች ሀገሮች ከተካሄዱት ታላላቅ ዐብዮቶች - እንደ 1789 ዓም-ኡ የፈረንሳይ ዐብዮትና እና እንደ 1917 ዓም የሩሲያው ዐብዮት - ጋር በአለም የጭቁን ሕዝቦች የትግል ታሪክ ተርታ የሚመደበውና የሚወሳው ታሪካዊው የሀገራችን የካቲት 1966ቱ ዓም አብዮት ከፈነዳ፤ ይኸው አርባ ሦስት ዓመታት አስቆጠረ። ይህ አብዮት፤ እንደአቻዎቹ ሁሉ ካያሌ ዘመናት የፍትኅ-ርትዕ መጓደልና የጭቆና አገዛዝ ከመነጨ የሕዝብ ብሶት የመጣ ነበር። ከኢትዮጵያ ሰቆቃ ማህፀን የተፈጠረ በመሆኑ፤ በዓይነቱ ወጥ ሆኖ ነገር ግን እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ የመጣ ስላይደለ ፤ ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ በነፃነት መበት መረጋገጥ ላይ ያተኮረ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነበር። ያልተደባለቀ፣ ያልተከለሰና የልተበረዘ ፤ በሁለንተናዊ ገፅታው ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ተጎናጽፎ የመጣ ነው። በመሆኑም ከእርሱ በፊት ከተከናወኑት የዓለም አብዮቶች ተርታ ተመድቦ ተገቢውን ቦታና ድርሻ አግኝቶ ተመዝግቧል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን አብዮት ከሌሎቹ የዓለም አብዮቶች ልዩ የሚያደረገው የራሱ ዓይነተኛ ባኅርይ የነበረው መሆኑ ነው። ከአነሳሱ ጀምሮ ሕዝባዊ አመፁ ሠላማዊና የብዙኃኑን ደጋፍና መሠረት ያደረገ ስለነበር ተከትሎ ሲንቀሳቀስ፤ አንዳችም የደም መፋሰስና የሕዝብ ዕልቂትም ሆነ የንብረት ውድመት በዋናነት ያልተከሰተበት ነበር። ከፍንዳታው አንስቶ እስከ ጥቂት የጊዜ ገደብና ሂደት ድረስ፤ ሠላማዊና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ስለነበረ፤ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጥፋትን አላስከለተለም ነበር ቢባል፤ ስህተት አይሆንም። ይህም ሁኔታ ሰላም ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ በሆኑ የአለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ አድናቆትንና ከበሬታን አስገኝቶ ነበር ማለት ይቻላል።

በነዳጅ ውድነት ምክንያት የተለኮሰው የታክሲ ሾፌሮች አድማ፣ በነገሌ ቦረና የተደረገው የጭቁን ወታደር የደሞዝ ጭማሪ እንቅስቃሴ፣ ለሶስት ቀናት ያህል የተካሄደው የላባደሩና የሠራተኛው እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም በወርሃ የካቲት 66 በአዲስ አበባ ከተማ ቁጥሩ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ በእስልምና ዕምነት ተከታዮች የተካሄደው ሠላማዊ ሰልፍ ከሁሉም ዕምነት ተካታዮች ድጋፍና ትብብር ማግኘቱ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ አቢይ ክስተቶች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን እስላሞችም፤ "ክርስቲያኑ ወገናችን፤ ተሰልፏል ከጎናችን ! " እያሉ በመዘመር ታሪካዊ ሠነዱን ማስመዝገባቸው ምንጊዜም የማይረሳ ትውስት ነው። ያ ታሪካዊ አብዮት፤ ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች አስተባብሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት በአዲስ መልክ ያስረገጠ፤ ዜጎቹን ሁሉ ያስተባበረ በመሆኑ፤ በዘመናዊቷ ሀገራችን ደማቅ ታሪክን አስመዝግቦ አልፏል። አንድ ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ በአዲስ አበባ ተሰብስቦ ሠላማዊ ሰልፍ ሲያደርግም በሀገሪቱ ታሪክ ጎላ ያለ ክስተት ሲሆን ሕዝብ

የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቅና ይሁንታ ሳያስፈልገው ያካሄደው ሠልፍ በመሆኑም፤ ሕዝባዊና ሰላማዊ ሰልፍ ምን እንደሚመስል፤ ለወደፊቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ትምህርትን ሰጥቶና አሻራውን አስቀምጦ ማለፉ በታሪክ መዛግብት ሰፍሮል።

ለብዙ ዘመን ታፍኖ እየተብላላ የቆየ ነበር ማለት ቢቻልም እንኳ፤ ይህ የየካቲቱ ሕዝባዊ የአመፅ እንቅስቅሴ በዱብ ዕዳ የመጣ እንደነበር ማንም አይክደውም። አመጣጡ ዱብ ዕዳ ነው የተባለው፤ ማንም ሳያስበውና ሳይተነብየው፤ ዕንግዳ ደራሽ በመሆኑ ነበር። የነበረውን አገዛዝና ሥርዓት ሁሉም ተቃውሞት ስለነበር የየካቲቱ አመፅ፤ ከሞላ ጎደል፤ የሁሉንም ኅብረተሰብ ክፍል ትብብርና ድጋፍ አግኝቷል። በዚህ ምክንያት፤ ኢትዮጵያዊ አንጡራ ማንነቱን አረጋግጦ ነበር የቀጠለው። በግብታዊ ባኅርዩ ላይ መሪ የሌለው መሆኑ ተደምሮበት ሁነኛ ባለቤት በማጣቱ፤ የጥቂት ምርጥ የጦር መኮንኖች ሰለባ ሆነ። ያ ግርማ ሞገስን ተላብሶ ሲካሄድ የነበረው አብዮት፣ ኃላፊነት በጎደላቸው ቡድኖች አቅጣጫውን ስቶ፤ ሕዝባዊ ቱማታውን ተነፍጎ፤ ተንገራግጮ ቀረ። የኅብረተሰብን አንድነትና ትብብር አግኝቶ የነበረው ሠላማዊ- ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፤ ደርግ ባስከተለው ሽብር ምክንያት ሀገሪቱ በደም አለባ ተጥለቀለቀች። ሕዝብ የጠየቀውን መሠረታዊ ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ በኃይል በማፈን፣ የሕዝብን እምቢ ባይነትና አመጽ ወደ እልቂት ገፋት ።

በመጀመሪያዎቹ ወራት፤ በሕዝባዊው አመፅ የተነሱት መሠረታዊ ጥያቄዎች ሁሉ በሥልጣን ጥመኞች አላዋቂነት እንዲኮላሹ ተደረጉ። ሕዝቡ ተስፋ አድርጎባቸው የነበሩ መሠረታዊ-ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በሕዝቡ እንቅስቃሴና ፍላጎት የተመሰረቱ አግባብ ያላቸው መፍትሔዎችን ተነፈጉ ። የመሰብሰብ፣ የመንቀሳቀስ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የማሰብ፣ የመወያየት መብቶች ሁሉ፤ ደብዛቸው ጠፋ። ደርግ፣ ባልተዘጋጀበት፣ ባላሰበበት፣ ባላወቀበትና የርዕዮት ግንዛቤ ባላገኘበት ሁኔታ ተዘፍቆ ለኢትዮጵያ ምስቅልቅል በር ከፈተ። "ታሪክ የጣለብኝን አደራ ለመወጣት" በሚል መወሽከት፤ እራሱን እያታለለ፤ ሕዝቡን ለማወናበድ ተጣጣረ፡፡ የደርግ ግርግርና ሽብር፤ የሀገሪቱን ውስጠ-ምሥጢር ከፍቶ ለተገንጣይ-አስገንጣይ አስረክቦ ሰጠ። ይኸንን አመች ሁኔታ ተጠቅመውም፤ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዕቅዳቸውን አሳኩ። በዚህም ምክንያት ዜጎቿም፣ የተነሱበትን የየካቲት አብዮትን ሀገራዊ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ለማቆየት በመገደድ፤ በሀገራቸው ጎልውና ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ምርጫቸው ሆነ። ተለዋጭ አማራጭ በማጣታቸው ምክንያት፤ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ሁሉ ተንገራግጨው ቀሩ።

በአንደኛ ምዕራፍ የተመዘገቡት የሕዝብ ጥያቄዎች ምን ነበሩ? ተብሎ መጠየቅ ካለበት፤ ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ነበሩ። መሬት ላራሹ! የብሔር ብሔረሰብ ዕኩልነት፤ የሃይማኖትና የሴቶች ዕኩልነት፤ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ ነፃነት ይከበር፤ ዳቦ ለተራበው! የድኻው ልጅ ይማር! የውጭ ጣልቃ ገብነት ተወግዶ የሀገራችን ሉዓላዊነት ይከበር! የማሰቃያና የአፈና ቤቶች ይዘጉ ! ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ገደብ ይረጋገጡ! የተባሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

ሁሉም ጥያቄዎች እስካሁን ተገቢውን መልሶች አላገኙም። ዛሬ መሬት በባለቤትነት ላራሹ ሳይሆን፤ በወያኔና በባዕዳን ተጠቃሚነት ዕጅ ሆኗል። ገበሬው የመሬት ባለቤት አይደለም የሥርዓቱ ተጠማኝ እንጂ። የብሔረሰቦች ዕኩልነት ሳይሆን፤ የአንድ ብሔር የበላይነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ሰፍኗል። ዳቦ ለተራበው መታደሉ ቀርቶ፤ እንዲያውም ቁጥሩ ወደ አስራ ስባት ሚሊዮን የሚገመት ረሃብተኛ ዛሬም በመላው ሀገሪቱ ላይ በጠኔ ይሰቃያል። ኢትዮጵያ ዛሬም እንደወትሮው በኃያላን መዳፍ ሥር መሆኗ ቀጣይ ሁኗል። የወህኒ ቤቶች ቁጥር ብዛት በትክክል የሚታወቅ አልሆነም። የሰብዓዊ መብቶችን ጥሰት መላው ዓለም አውቆ መዝግቦታል። የስደተኛው ብዛት መላውን ዓለም አጥለቅልቆታል። የሀገሪቱ ዳር ድንበር ተጥሷል። ሉዓላዊነቷ ተደፍሯል። በብዙ ኪሎ ሜትር የሚመተር መሬቷ ለባዕድ አሳልፎ ተሰጥቷል። የባህር ወደብ የለሽ ሀገር ሆናለች። በሃብታሙና በድኻው መካከል የሚታየው ልዩነትና ስፋት አሰቃቂ ደረጃ ደርሷል። ዜጎቿም በቋንቋ፣

በዘርና በጎጥ እንዲከፋፈሉ፤ እንዲያዩና እንዲያስቡም ጥረት ተደርጓል፤ እየተደረገም ነው። የሀገሪቱ ያሁኑ አገዛዝ የፖለቲካ መሠረቱ የጎሣዊ አገዛዝ አስተናጋጅነቱ ልዩ መለያው ሁኖ እየቀጠለ ነው። በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በመላው ዓለም በመሰደድ ላይ ናቸው፤ እስከዛሬም በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ በየምደረ-በዳው ተቃጥለው ጠፍተዋል፤ ወጣት እህቶቻችን የአስገድዶ መድፈር ሰለባ ሁነዋል፤ አንዳንዶቹ ጭካኔ በተሞላበት ቀዶ ጥገና የውስጥ አካላቸው ተወስዶባቸዋል። ሌሎቹም የአሣነባሪ ዕራት ሆነው ቀርተዋል። ይኸ ሁሉ ስቃይ የደረሰው፤ ለአለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት፤ መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችን/ፍላጎቶችን ከመመለስ ይልቅ የአንድ ጎሳ የዘር ፖለቲካ ያመጣው ጠንቅ ነው።

ሲጠቃለል፤ የየካቲቱ ስድሳ ስድስት አብዮት ሕዝባዊ ጥያቄዎች ሳይመለሱ፤ ተኮላሽተውና ተዳፍነው መቅረታቸውን ነው አስምሮ ማስቀመጥ የሚቻለው። ከላይ የተዘረዘሩት፤ ዋና ዋና ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች፤ ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ ዓይነተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው። በቀጣይነት የሚጠየቁ በመሆናቸው፣ ባስቸኳይ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል። ካልተመለሱ ግን፤ የሕዝብ አመፅ ይመልሳቸዋል። ያስመልሳቸዋል። የሕዝብን ጥያቄ አድበስብሶና አኮላሽቶ ለብዙ ጊዜ ማስቀረት አይቻልምና።

የ66 አብዮት ከመፈንዳቱ ሁለት ዓመት በፊት አስቀድሞ ፤ በሚያዝያ 1 1964 ዓ ም ኢሕአፓ የተወለደው ፤ ከላይ የተዘረዘሩት ዘርፈ-ብዙ የሀገሪቱ ችግሮች አፍጥጠው- አግጥጠው ብቻ ሳይሆን ፤ ከቁጥጥር ውጭ ሆነው በመውጣታቸው ምክንያት፤ አስቸኳይ መልስ በሚጠይቁበት ታሪካዊ ወቅትም ነበር። የነበረው ሥርዓት፤ ምንም ዓይነት ተቃዋሚ በማይፈቅድበት ወቅት የተመሠረተው ፓርቲ ፤ ራዕዩ ሰፊ ፤ ዓላማው ፅኑ ፤ ተግባሩ ግዙፍ ፤ ሀገራዊና ሕዝባዊ ፍቅሩ እንከን የማይወጣለት መሆኑን በማብሰር ትግሉን ጀመረ። ትግሉ፣ እልህ አስጨራሽና መራራ ፤ ከባድ መሥዋዕት አስከፋይ፤ ጉዞው ውስብስብና ረዥም መሆኑንም ተረድቷል። ኢትዮጵያና ሕዝቧ፤ የዴሞክራሲ ጮራ ፍንጣቂ ማግኘት አለባቸው ብሎ የጀመረው፤ የወጣትነት ተስፋውን ሰንቆ በመነሳት ነበር። ይኸንን ተስፋውን ቋጥሮ እየተሰናዳ ባለበት ወቅት ነበር፤ የየካቲቱ አብዮት በግብታዊነት ከተፍ ያለው። ይህም በቂ መሠረት ጥሎ ለመራመድ ፓርቲው ሰፊ ዕድልና በቂ ጊዜ አላገኘም። ያም ሆኖ ግን፤ ሕዝባዊና ሀገራዊ ፍቅሩን መሠረት አድርጎ አብዮቱ ያመጣውን ኃላፊነት ተረክቦ መታገሉን ቀጠለ። ሀገሪቱን ከጭቆና ዜጎቿንም ከብዝበዛ ለማላቀቅ ፤ የመጀመሪያው ተግባር እንደሆነ አምኖም ነው የተንቀሳቀሰው። ይህ ተግባር ከባድ ኃላፊነት የሚጠይቅ መሆኑን ቢረዳም፤ ግዴታውን ለመወጣት ወደ ኋላ ሳይል አቅሙ የፈቀደለትን ሁሉ ፈጽሟል። የሕዝቡን ትግል ፈር ለማስያዝ ፤ የሚጠበቅበትን በሚቻለው አከናውኗል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን፣ የሚታፈርባት ሀገር እንዳይደለች ለማስመስከር የተቻለውን ሁሉ ጥሯል። ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ብቻ ሳትሆን፤ ታላቅ ትምህርት ቤታችንም ስለሆነች ብዙ አስተምራናለች። ሰፊና ጥልቅ ዕውቀትን ለግሳናለች። አሳይታናለች። ክፉውን ከደጉ ለይተን እንድናውቅ ረድታናለች። በዚህ ምክንያት፣ ለሀገራችንና ለሕዝቧ የሚኖረን ፍቅር፤ ዘመን ተሻጋሪ ነው። የትግላችን መሠረቱም ይኸ ነው። በገዋ ላይ ተቀምጠው፤ በሕዝብ አናት የሚንሳፈፉ መፈክሮችን ማቀንቀን ሳይሆን፤ የሕዝቡን ስሜት በትክክል የሚያስተጋቡና ምኞቱን የሚያንጸባርቁ መሠረታዊና ወቅታዊ ችግሮቹን የሚመለከቱ መፈክሮችን አንስቶ እንታገል በማለቱ ፤ ኢሕአፓ የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍና ትብበር አግኝቶ እንደነበር ታሪክ የመዘገበው ዕውነታ ነው። የገባውን ሀገራዊ ቃልኪዳን ጠብቆ እስካሁን ድረስ በመታገል ላይ መሆኑም፤ አብነቱ ይኸው ነው።

የዴሞክራሲ ዓይነተኛ ዓላማ አንዱ፤ ሕዝብ ያላንዳች ገደብ በነፃ የመደራጀት መብቱን ማግኘት አለበት የሚለው መርህ መሆኑ አንድና ሁለት አይባልም። ፓርቲው ይህንን ዓላማ በማንሳቱ፤ የደርግ ከይሲ ዒላማ ተነጣጠረበት። በአንደኛ ጠላትነት ተመዝግቦ፤ መጥፋት አለበት ተብሎ ተፈረጀ። የማጥፋት እርምጃም ታወጀበት። ምርጥ መኮንኖቹም የሀገሪቱን

ውስብስብ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች፤ በጥይት እሩምታ፤ በአዋጅ ጋጋታ የሚፈታ መስሏቸው፣ ሲዳክሩ ቆይተው ፤ ሳይሆንላቸው በመቅረቱ፤ ሀገሪቱን በትነው፣ ከነአቀንቃኞቻቸው እንደ ጉም በንነው ቀሩ። ይኸ እንዳይከሰት አማራጭ መፍትሔ ማምጣት አስፈላጊ መሆንን አስቀድሞ የተረዳው ኢሕአፓ፤ በአብዮቱ ወቅት፣ ከማንኛውም ጉዳይ በፊት፤ "ከሁሉም ኅብረተሰብ የተውጣጣ ጊዚያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት" ብሎ አሳወቀ። ለጊዚያዊ ሥልጣን የቋመጠው ሁሉ ሳይቀበለው ቀረ። ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ተመሥርቶ፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን ለደረሰችበት አደጋ ምክንያት ሆኖ፤ ለፀረ-ኢትዮጵያ ክፍሎች መሠረት ጣለላቸው። ፓርቲው፤ ከሁሉም የተውጣጣ ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የመቋቋሙን አስፈላጊነት ያስረዳው በሚከተሉት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበር።

**1**ኛ. የሀገሪቱን ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የወደፊት ዕድሏን ለመቀየስ ወሳኝ መሆኑን አስቀድሞ መገንዘብ ጠቃሚ ከመሆኑ አንፃር፤ ሠላማዊና የተረጋጋ የፖለቲካ ሽግግር ወቅት መፈጠር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ነበር። ከዚህ ሐቅ በመነሳት፤ ከሁሉም ኅብረተሰብ የተውጣጣና መከላከያ ሠራዊቱንም ጭምር የሚወክል ጊዚያዊ መንግሥት ከመጣ፤ ሀገሪቱን ከተቃጣባት አደጋ ሊያድናት ስለሚችል ነበር።

**2**ኛ. ሠላማዊ-ሕዝባዊ ሽግግር ከተካሄደ፤ ሁሉ ዜጋ ያለስጋትና ፍርሃት የሀገሪቱንና የራሱን የወደፊት እጣ አስመልክቶ ሙሉ ተሳታፊ የመሆን ዕድሉ የተሟላ ይሆንለታል። በመሆኑም የባለቤትነቱና የሙብቱ ዋስትና ዕውን መሆኑ ይረጋገጥለታል። ማንኛውም ዜጋ በሂደቱ፣ ኅብረተ-ሱታፌውን ካረጋገጠ ደግሞ ሕዝባዊው እንቅስቃሴው የሁላችንም ነው ብሎ ስለሚያምን፤ ገደብ -የለሽ ለሆነ ዴሞክራሲ መሠረት ለመጣል ሁኔታዎቹን ያመቻቻል። ይህ በበኩሉ፤ ዜጎች የመደራጀት መብትና ነፃነታቸውን ከማንም ሊጠይቁ አይችሉም። ዴሞክራሲያዊ ነፃነትን አስመልክቶ፤ ለማኝና ተለማኝ፣ ሰጭና ነሺ፤ ነጣቂና ተነጣቂ ፤ ገፍታሪና ተገፍታሪ አይኖርም። በራስ የመተማመን ብቻ ሳይሆን፤ ሁሉም ዜጋ በኢትዮጵያዊነቱ የመኩራትና የወደፊት ዕድሉን ራሱ የመወሰን መብቱን ያረጋግጥለታል። የሀገሩን ጥቅም በጋራ የማስከበር ግዴታውን የመወጣት የዜግነት ኃላፊነት ይኖርበታል።

**3**ኛ. ኢትዮጵያ፣ የራሷ የግሏ ታሪክ፣ ባህል ዕምነት፤ መስተጋብርና ዕሴት የነበራት ሀገር መሆኗን ብቻ ሳይሆን፤ የመንግሥት ሥርዓቱም ኋላ ቀር የሆነ ንጉሳዊ አገዛዝ ስለነበረ፤ በዚህ ሥርዓት ማኅበር ስር ለሚማቅቅ ኅብረተሰብ፤ አብዮትን ማስተናገድ የሚገባው ሁሉንም ባካተተ የሽግግር ሂደት መሆን እንደሚገባው በመገንዘብ ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረችዋ ኢትዮጵያ በጊዜያዊ ሽግግር መንግሥት መተላለፍ፤ ዘላቂ ዕድሏን ለመቀየስ በቂ ጊዜ ማግኘት ወሳኝ እንደነበር ታምኖበታል። ከሕገ-መንግሥት አቀራረጽ አንስቶ ፤ ምን ዓይነት ሥርዓተ መንግሥት ሊኖራት እንደሚችል - አሃዳዊ ወይስ ፌዴራላዊ አወቃቀር? ፌደራላዊ ከተባለስ፤ እንዴት ዓይነት የፌዴራል አወቃቀር ይኑራት ? የሚለውን ሁሉ አካቶ ለመወያየት ፤ በግድ ሠላማዊና የተረጋጋ ሽግግር ማካሄድ እንደነበረባት ፓርቲው አስቀድሞ መጠቆሙ ፤ ካርባ ዓመት በኋላ ሀገራችን ዛሬ እምን ላይ እንዳለች ቋሚ ምስክር ሆኗል።

ከላይ ከአንድ እስከ ሦስት ተራ ቁጥሮች ከተዘረዘሩ አሳማኝ ምክንያቶች በመነሳት፤ ሁሉን ያካተተ ሕዝባዊ ጊዚያዊ የሽግግር መንግሥት እንዲመጣ ግዴታ ነበር እንጅ ሌላ የተሻለ አማራጭ አልነበረም። ፓርቲው ዛሬ ይኸንን ማንሳቱ፤ "ተናግሬ ነበር፤ የሚሰማ ጠፍቶ ነው እንጅ" ብሎ ወዳሴ ከንቱን ለማስተናገድ ሳይሆን፤ ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ከዓርባ ዓመት በኋላ ዛሬም እንደ አዲስ ሆኖ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ መልከዓ-ምድር ብቻ ሳይሆን፤ ተጨባጭ ሁኔታውም አስገዳጅ ጥያቄ አድርጎ እያመጠው ስለሆነም ጭምር ነው። ወቅታዊው የፖለቲካ ምኅዳር የሚጠይቀውም ይኸንኑ ነው። ተወደደም ተጠላ፤ ወቅታዊው የፖለቲካ ምኅዳር በዋናነት የሚጠይቀው ጉዳይ ቢኖር፤ ሁሉንም ያሳተፈ የሽግግር ወቅት አስፈላጊነትን ነው።

ዛሬ ወያኔ በፈጠረው ቀውስ ምክንያት፤ በሀገሪቱ ሠላምና መረጋጋት አለ ተብሎ አይታሰብም። ዘረኛው አገዛዝ በወለደው ሽብር ምክንያት ሰላምና ማኅበራዊ መረጋጋትን አጥታ መላ ሀገሪቱ በተለያየ የሕዝባዊ አመጽ እየተናወጠች ትገኛለች። ይህም ሁኔታ ወደማያባራ ሁከትና ቀውስ እንድትገፋፋ አድርጓታል። ሁኔታዎቹ ሁሉ በዕውር-ድምብር ይጓዛሉ፡፡ በዚህም የተነሳ በተለይም ሀገር ተረካቢ የሆነው በርካታ ወጣቱ ዜጋ ከሀገሩ እየተሰደደ በመሄድ ላይ ነው። ሁለት ተጻራሪ ኃይሎች በአቻ ለአቻ ደረጃ ናቸው ለማለት ባያስደፍርም ፤ በፖለቲካ ምኅዳሩ የሰፈሩ ፖለቲከኞች ነን ባዮች፤ ወገን በመለየት ተፋጥጠው ቆመዋል። እነርሱም፣ አሁን ያለውን ቀውስ በበለጠ እንዲባባስ አድርገው፤ ሀገሪቱን ወደ አደገኛ ፀድፍ በመግፋት፤ ሕዝብን ማፋጀት የሚሹ፤ ወያኔና ሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድኖች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፤ እነርሱን ተጻርረው የቆሙ፤ የሀገር ኃላፊነት የሚሰማቸውና ኢትዮጵያን ከመበታተን አደጋ ለማዳን የቆሙ የአንድነት ኃይሎች ናቸው ማለት ይቻላል።

የአንድነት ኃይል ናቸው የሚባሉት ክፍሎች፤ ሠላማዊ የሽግግር ወቅትና ሂደት መምጣት አለበት ብለው ያምናሉ። ይኸ ዕምነት መሠረታዊ በመሆኑ፤ ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት ሊያስገኝ የሚችል ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያሳትፍና አስተማማኝ ሁኔታን ያመጣል ተብሎም ይታመናል። በአሁኑ ወቅትም በየካቲቱ ወቅት ተጠይቆ እንደነበረው፤ በኢትዮጵያ ላይ የተንሰራፋው ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ፤ በሕዝብ በነ ፈቃድና ሙሉ ተሳትፎ የሚመሠረተውን ሥርዓተ-መንግሥት እውን ለማድረግ፤ ሀገሪቱ በሽግግር ሂደት ውስጥ እንድታልፍ የግድ ይላል።

መልካም አዝመራን ለማምረት ፤ መጀመሪያ ማሳውን ከአረምና ሙጃ ነፃ ማድረግ እንደሚገባ ሁሉ፤ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ አስተዳደር ለመትከል፤ ካስፈለገም፤ የሀገራችን ፖለቲካ መልከዓ ምድር፤ ማሳው ተደላድሎ፣ ለስልሶ፣ ከእሾኽ-አሜካላ ነፃ እንዲሆን መፅዳት አለበት። ሊፀዳ የሚችለውም፤ በሽግግር ወቅት ሂደት ወስጥ ነው። ይኸ ሥር የሰደደ የሀገሪቱ ችግር፤ ዘላቂ በሆነ መልኩ ሊፈታ የሚችለው፤ በሕዝብ በነ ፈቃድና ሙሉ ተሳትፎ እንጅ፤ ቀውስ አንጋችና ግርግር ጠንሳሽ በሆኑ አልፎ ሃጂዎች አይደለም። "ኢሕአዴግ መራሹ !" እያሉ ቢያቆለጳጵሱት የሀገራችን ችግር ፍንክች የሚል አይሆንም። መሠረታዊ ለውጥ መምጣት፤ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔን ያስገኛል። ዘለዓለማዊት ለሆነች ሀገር፤ የሚያስፈልጋት ዘለዓለማዊ መፍትሔ እንጅ፤ አጋጣሚውን በመጠቀም ሥልጣን ላይ በሚወጡ ለሕዝብና ለሀገር ደንታ በሌላቸው የሱቅ በደረቴ-ነጋዴዎች፤ የአየር-በአየር ደላላዎችና አቀባባይ ከበርቴዎች አይደለም።

ችግራችን፤ ዘርፈ-ብዙና ውስብስብ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ እየተንከባለለና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ እስካሁን ቀጥሏል። ተወራራሽ ሥርዓቶችና ትውልዶች የየራሳቸውን የቤት ሥራ በሚገባ ባለፈፀማቸው ምክንያት ፤ ችግርና መከራን፤ እያወረሱ ይሄዳሉ። ኢሕአፓም የችግርና የመከራ ወራሽ ከመሆን አላመለጠም። ካለፉት አርባ ሦስት ዓመታት ጀምሮ፤ ታሪክ የጣለበትን ዜጋዊ ኃላፊነት ለመወጣት አቅሙ የሚፈቅድለትን ሁሉ ፤ ያለሃኬት እየጣረ ይገኛል። ይኸንን በማድረጉ፤ በውስጥና በውጭ የሀገሪቱ ጠላቶች በኩል ተነግሮ የማያልቅ በደልና ግፍ ተፈጽሞበታል። በህሊናውና በጎልውናው ላይ ከባድ ከባድ ፈተናዎች ተፈራርቀውበታል።

በተለይም ደግሞ፤ ተገንጣይና አስገንጣይ ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድኖች ተባብረው ብርቱ ጥፋት ሊያደርሱበት ሞክረዋል። ሁሉንም እንዳመጣጣቸው ተቋቁሟቸዋል። ሁሉም ፓርቲውን ዒላማ ለማድረግ የተገደዱት ፤ በሀገራዊና በሕዝብ አንድነት ላይ ሊደራደር ባለመቻሉ ብቻ ነው። ፓርቲው፤ መሠርታዊ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የኢትዮጵያን ኅልውና የሕዝቧንም አንድነትና ነፃነት በዕኩልነት መከላከልና ብሄራዊ ጥቅሟንም ማስጠበቅ በመሆኑ ፤ የትግሉ አልፋ- ዖሜጋ አድርጎት ዘልቋል። የኢሕአፓ ታጋዮች፤ የትግላቸው መልኅቅ፤ ኢትዮጵያ ብቻ ነች ። ሌላ ጉዳይ የላቸውም ። ከኢትዮጵያና ከሕዝቧስ የበለጠ ሌላ ምን ጉዳይ ሊኖራቸው ይችላል ?

የሀገሪቱን ዘርፈ ብዙ ችግር ማሰወገድ ተቀዳሚ ዓላማ መሆን አለበት ሲባል፤ ከሁሉ አስቀድሞ ሊጤን የሚገባው፤ የሕዝቧ ስብጥር፣ ታሪኳና ባኅሏ፣ ጠባይዋ ዕምነቷ፤ የሀገሪቱ መልከዓ ምድር (ጂኦግራፊ) እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብቷንም ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። ይኸንን ሁሉ አካትቶ የሚያስተናግድ መፍትሔ መፈለግ፤ ፍትኃዊና ፍቱን ይሆናል። የብዙሃን ብሔር ብሔረሰቦች ምድር እንደመሆኗ፤ የመፍትሔ አፈላለጉም ቅየሳ ይህንኑ መሠረት ያደረገ መሆኑ ሊያከራክር አይችልም፤ አይገባምም። ይኸንን ሐቅ ተቀብለን ከተነሳን፤ ሁሉ አቀፍ ዴሞክራሲያዊና አንድነትን በዕኩልነት ያቀፈ መፍትሔ ከመፈለግ ሌላ አማራጭ አይኖርም። ይህ እስካሁን አልተሞከረም። አልተፈተሸም። እስከዛሬ ሲደረግ የነበረው፤ በጠብመንጃ እያስፈራሩ የግል ፍላጎትን ብቻ ማርካት ነበር፡፡

ከእንግዲህ ወዲያ፤ ይህ ሊቀጥል አይገባም። እኔ ብቻ አውቅልሃለሁ መባሉ ቀርቶ፤ ሕዝባችን አንተው እራስህ፤ ለራስህ ዕወቅበት-ዕወቅለት ሊባል ይገባዋል። ከበይ ተመልካችነት ወጥቶ፤ የራሱና የሀገሩ ዕድል ወሳኝ ራሱ ሕዝቡ መሆኑ መረጋገጥ ግድ ሊሆን ነው። ይኸ ዕውን እንዲሆን ከተፈለገ፤ ገደብ የለሽ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት በመላው ሀገሪቷ መስፈን አለበት። መስፈን አለበት ማለት፤ ሕዝቡ ሉዓላዊነቱን ማሰከበሩን ማረጋገጥ አለበት ማለት ነው። ይኸንን የሚያረገግጠው ደግሞ፤ ራሱ በቀጥታ የተሳተፈበት የባለቤትነት ዋስትናውን፤ የሥልጣን ምንጭነቱን ሲያገኝ ነው። የዚህ ዓብነት፤ ሞግዚት-የለሽ ተሳትፎውን ሲያረጋግጥ ይሆናል።

ዴሞክራሲ አመርቂና አስተማማኝ ሕዝባዊ ቦታ እንዲጎናፀፍ ከተፈለገ፤ የዜጎቹ ቀጥታና ሙሉ ተሳትፎ ዕውን ሊሆን ይገባል። የዴሞክራሲ አቅራቢ ሞግዚት፤ የአጋፋሪ ሕገ መንግሥት አርቃቂ፤ ጦር መሣሪያ ታጣቂ የሕዝብ ሙብት ጠባቂ ፤ የሚባል ቀልድ ሊኖር አይገባም። ሁሉም ዞሮ ዞሮ የአምባገነን ገዥዎች አካል/ አገልጋይ ከመሆን አያልፉም ። የታየውና ተመክሮም ያረጋገጠው ይኸንኑ ነው ። ተዋናዮቹ ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፀር ናቸው ።

የሕዝብ ዕውነተኛና ታማኝ ወዳጅ የሚመነጨው ከሕዝብ ማህጸን ውስጥ ነው። ታሪክም ይህን ሐቅ ደግሞ መስክሮለታል። በአንፃሩ ደግሞ፤ በዓለም ታሪክ ሂደት፤ ኃሳዊ መሲሆች በየጊዜው እየተነሱ፤ በሃይማኖት ስብከት፣ ሥልጣኔን በማስፋፋት፣ ሀገር በማቅናት፣ ርዕዮተ-ዓለም በማስራጨት፤ ነፃነትን በማግኘት ሰበብ ብዙ ግፎች ተፈጽመዋል። ኢትዮጵያ ሀገራችንም የእነኝህ ሁሉ ግፎች ሰለባ ሆናለች። በስርወ-ሶሎሞን፣ በሶሻሊዝም ዳንኪራ፣ ዘረኞች ባመጡት የዘር ቆጠራ፣ ...ወዘተ ባጠቃላይ ሁሉም ባመጡት ጣጣ የተለያዩ ግፎች ሲፈራረቁባት ቆይታለች።

ምናልባት ወደፊትም፣ በዴሞክራሲ ስም፤ አዲስ ውሃ ያልነካው ግፍ ሊፈፀምባት ይችል ይሆናል ? ሕዝቡ ነቅቶ ተደራጅቶ ፤ አውቆ ጠንቅቆና መጥቆ እራሱን ነፃ ካላወጣ፤ የሚያንዣብበው አደጋ ቀላል አይሆንም። ከኢሕአፓ ተቀዳሚ ተግባራት መካከል አንዱ ፤ በሀገርና በሕዝብ ላይ ሊመጣ ይችላል ብሎ የታየውን ማናቸውንም አደጋ ለሕዝብ መግለፅ ስለሆነ ከየካቲት ስድሳ ስድስት አብዮት ጀምሮ ይህንን ከማድረግ አልታከተም። ወደፊትም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ፤ ይኸንን ማስጠንቀቁን ይቀጥልበታል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ከሚታየው ጠቅላላ ገፅታ አንፃር፤ የጠላቶቿ ሴራ ተሳክቶላቸዋል ከማለት አንቆጠብም። ይህን ስንል፣ የነርሱ ብርታትና ብልሃት ሳይሆን ፤ የራሳችን ድክመትና እንዝህላልነት ያስከተለብን ጣጣ ነው። እንዲያውም የሀገራችን ጠላቶች ብዙ ሳይደክሙ፤ የፈለጉት ተሟልቶላቸዋል፡፡ ይህን ዕውነታ፤ እንደ እንቆቅ እያንገሸገሸን ነው የምንናገረው። ዘጠና ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ፤ የአንድ ሰፈር ልጆች መጫወቻ ሲሆን ማየት፤ እጅግ ሲበዛ ያንገፈግፋል። የስድሳ ስድስቱ አብዮት ዓላማና ግቡን ሳይመታ ትግላችንን አናቆምም ስንል ፤ ከዚህ የማይፋቅ ዕውነትና ዕምነት በመነሳት ነው። የዕምነት ግማሽ

የታሪክ ቅናሽ የለንም። ወያኔ በውጭ ኃይሎች የእዝ ጠገግ ሥር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የዛፍ ላይ ዕንቅልፍ የሚያንጎላች ቡድን በመሆኑ፤ ቅዠት እንጅ ህልም እንደሌለው እናውቃለን ። በቅዥት የሚኖር ስብስብ በመሆኑም ሌላውን ቀርቶ፤ የራሱን ጥላ እንኳ የሚፈራ ቡድን ነው ። ማንንም ሊያምን አይችልም። እውነት መልኳን ብትለውጥ እንጅ ፤ ጠባይዋን ስለማትስት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን ቆማ፤ ሀቁን እየተናገረች ሀገራዊ ድሉን ታበስራለች! ያ ድል እስከሚመጣ ድረስ ትግላችንን እንቀጥላለን !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል !